# ጣዕመ መረቅ

መድህን ፀጋዬ

Jan 2015

(ስለ እፎይታ፣ ስለ ብድር ማቃለል ለራስ…ስመጻፍ እንደተሞከረ ይሁን..)

## መረቅ እንደምን ተሰማኝ (How Mereq makes me feel)

በመጀመሪያ ስለ መረቅ የመፃፍ ደስታዬ ከማንበብ ጉጉቴ በዝቶ ይመስለኛል ጉጉቴ ቢያስገበግበኝም እንኳን ለብዙ ሰዓቶች ሳገላብጥና ሳፈጥበት ማንበብ አቃተኝ፡፡ የምሄድበት ቦታ ሁሉ እጄ ላይ አለ ብቻዬን ሆኜ ለሻይ እረፍት ሳደርግ ላነበው አስቤ ከእጅ ቦርሳዬ ውስጥ አወጣዋለሁ….አየዋለሁ…..አገላብጠዋለሁ….የእለት ጣጣዬ ዙረቴ አልቆ ለመተኛት ስሰናዳና መተኛዬ ላይ አረፍ ስል እገልጠዋለሁ፡፡ ማንበብ ግን አልቻልኩም፡፡ እንዲህ ለብዙ ቀን ሆነ (3/4) በአሰልቺ ስብሰባዎች መካከል በመጀመሪያው የሻይ እረፍት እንዲሁ ገለጥኩ፡፡ ቢያንስ ስለምን እንደታፃፈ ለማወቅ ያመቸኝ ዘንድ በማሰብ ማገለባበጤን ቀጠልኩ ስጦታ....ይዘት....Highlighted የሆኑ መዓት ቃሎች...ስዕሎች...ስለ እንጀራ ገለጣ መግቢያ...ምን አልኩ እሱኑ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ከታሪኩ ፍሰት ጋር የማይገናኝ መሆኑን ስረዳ ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡ መደመሜ የልቤን ሞት ተከትሎ በሁሉ ሰውነቴ ሲገባ ይታወቀኝ ነበር፡፡

## ስሜት

### ስለ እንጀራ ገለጣ መግቢያ

*መጀመሪያ ርዕሱን ሳነብ ምን መሰለኝ በግራጫ ቃጭሎች የመጀመሪያ ገፆች ላይ ስለ እንጀራ እንደተገለፀው መረቅ ልክ እንደ እንጀራ የመፃፊያ ስልት ሆኖ የመጣ.. ስለዚህ አዲስ ስልትም የሚብራራ…ማለት በእንጀራ ህጽናዊነት እንደቀረበ ሁሉ ሌላ አዲስ የአፃጻፍ ስልት* (method or theory) *ወይም ራሱ ህጽናዊነት በሌላ ቅርፅ* (form) *የሚቀርብ….እያነበብኩ እየወረድኩ ስመጣ ያሰብኩት እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡ ፍፁም ባላሰብኩበት መንገድ ግን በምጠብቀው የስሜት ነውጥ ውስጥ ገባሁ፡፡ የእውነት ተገረምኩ፡፡ በጣምም ደስ አለኝ፡፡ ሁልጊዜ እንደሚቀናኝ ስለ አዳም አመሰገንኩ፡፡ ደግሞ የእንጀራ ገለጣው ነገር ያስቃልና ፈገግ እያልኩ በሁነቴ ውስጥ ሆኜ ከባድ ነገር ለማንበብ እንደገለጥኩ ተገንዘብኩ፡፡ ዝርዝር የተቀናጀ ትረካዬን ልተውና እንዲሁ ላፍስስ፡፡ ስለ ሸሮ ሜዳ. . . እናኑ…አላዛር….ቴቢ…. ስለ እዝራ…ስለ ማኩዳ…*

### ልጅነት

*ልጅነት. . . እንደ ሁልጊዜው እያማረኝ ጓደኞቸው እንደሆንኩ ሁሉ እየተሰማኝ ልጅነቴ ሁነቱ ሙሉ ባይገጥምም ልክነቱ እየታየኝ. . እነ አላዛር የጥሩ ጊዜ ስስቴን በናፍቆት እያስታወሱኝ. . .ብዙ እየሳኩኝ. . .ምንም ሳልተከዝ. .*

**እናኑ**

. . . የሰብለ ተመልሶ መምጣት ከተጋደምኩበት አነቃኝ፡፡ አይኖቼን ከፍቼ ቁጭ አልኩ፡፡ የምወዳት የምታሳሳኝ በህይወት ያለች አያቴ በብዙ ነገር ከእናኑ የምትመሳሰል ናት፡፡ በደግነቷ፣ በአዋቂነቷ. . በሸንኮራ ፍቅሯ፡፡ ከአያቴ በመመሳሰሏ ሳይሆን እናኑ በራሷ የምትገዛኝ ነበረች፡፡ ነዋሪ ሳትሆን እንደ ህይወት ናት፡፡

1. የሰብለ መምጫ መንገድ እናም የዋናው ተረከኛ የአላዛር መገኛ መሆኗ
2. የሸሮ ሜዳ ባለርስት ነበረችና....ለሁሉ ቤተሰብ በአላዛር ዙሪያ ለነበሩ የታሪኩ አካል እነ እዝራ፣ ማከዳ፣ ቴብ፣ አልማዜ. . .) መኖር በቀጥታ በተዘዋዋሪም ሳይሆን እንደ ምንጭ (Source) በመሆን፡፡ ማለቴ ለምሳሌ የሸሮ ሜዳ ርስት የገዛ እራሷ ነውና ቤቶች ተሰርተው ሰው የሚኖርባቸው ሰፈር ሳይሆን እርሻ ይሁን ብትል ሸሮ ሜዳ የሚባል ሰፈር የለም፡፡ የሚወራ ታሪክም አይኖርም፡፡ የብዙ የሌሎች መሆን ሲችል የሸሮ ሜዳ መሬት የሷ እንዲሆን ተደርጎ መቅረቡን ላስተዋለ ብዙ ነው፡፡
3. ሌላ የመረቅ ስሪት ዘዬ እና ፍልስፍና ወይም plot (አንጓ መለልታና መረቅ) ከእሷ ልዩ የሸንኮራ ፍቅር እና አስተያየት መቀዳቱ (drive) መደረጉ፡፡

እነኚህ ሁሉ በአጠቃላይ በሆነችው በምታወራው ማለት ስለ ህይወት ባላት አመለካከት ስለኖረችው ኑሮ ስለ ተገነዘበቻቸው እውነቶች ከምወዳትና ከምታስገርመኝ በላይ እንደ የጀርባ አጥንት (spinal cord) ለአጠቃላይ የመፅሐፉ ቁመና መሰረት ሆና አግኜቻታለሁ፡፡ ይህም አይኖቼን በግርምት ከፍቷል፡፡

**ሰብስ**

የሰብለ መሸሻ ከፍቅር እስከመቃብር ከሞት ወደ ዳግም ህይወት መምጣት. . .ሀሳቡ፣ መንገዱ፣ አሰራሩ/ስልቱ (the technique)…ጊዜና ቦታው፣ ሂደቱ. . . ደግሞ በፍቅር መውደቋ ….ባትጋባም መውለዷ. . .ሰውየው አርመናዊ መሆኑ…መሞቱ ፍፁም ያልጠበኩት ደግሞ የእውነት ደስ ያሰኘኝ ነበር፡፡

1. አዲስ አቀራረብ (Approach) በመሆኑ፡፡ በትንሽ የንባብ ልምዴ እስካሁን እንደዚህ አልገጠመኝም
2. ስለ ደራሲው ወይም በአጠቃላይ ስለድርሰት ነፃነት፣ ዳርቻ (scope)፣ እና spontaneity አዲስ አይነት ግንዛቤና ትምህርት መሆኑ፡፡

በመጀመሪያ የጥቂት ገፅ ንባቤ ጠይቄ ለመረዳት ብሞክርም እንኳን ጥያቄ ሆኖ የቀረብኝ የሰብለ ለአላዛር አያት ሆኖ መመረጥ አስፈላጊነት መፅሐፉን አጠናቅቄ ካነበብኩ በኋላ ሳስበው የማይሆን ሆኖ አላገኘሁትም

1. ስለህጽንነት፡- የሷ የተሰበረ የፍቅር ህይወት (ከፍቅር እስከ መቃብር ጀምሮ) ለእናቱ ሮዚ ደግሞም ለራሱ ለአላዛር እንደ ንግርት አይነት ሆኖ በተሰበረ ልብ ወይም ባልታሳካ የፍቅር ሕይወት ህጽናዊነት ሶስቱን ያገናኘ ሆኖ ተሰምቶኛል ማለት ልክ የሃላፊ ጊዜ ህፃናዊነት ትስስሮሽ (network) እንደ ገመድ ብናበጅ ሶስቱ እንደ ቀጫጭን የገመዱ ጉንጉን ባለ ቅርርብ ይጠላለፋሉ፡፡ ሌላ እኛን አንባቢዎቹን ለሶስቱም አንድ አይነት በሆነ የሀዘን ስሜት ያገናኝናል፡፡ ከሌሎች የአገራችን ደራሲ የልብ ወለድ ስራዎች ለፍፁም ፍቅር ግን ደግሞ ላልተሳካ ፍቅር በዛ ዘመን መቼት እንደሰብለ አይነት መምረጥ እና ማውጣት የሚያስቸግር ይመስለኛል፡፡

2. የአላዛር ቆንጆ አይነግቡ መልክ፣ ቀና ባህሪ ደግሞ ስሜት… በሚያውቁት ሁሉ፣ በጓደኞቹ ይልቁንም በተባረኪ አይኖች እንደ እሴት አይነት ዋጋ የነበረው ነውና ሰብለ ስለ ውብ መልኳ ስለ መልካም ባህሪዋ እና ስአርመናዊ ፍቅረኛዋ በዚህም የሁለቱም ተስተካካይ ሆና ስለተፈጠረች እናቱ ሮዛ ስለ አላዘር ተፈጥሮ ግድ ሆና ትገኛለች፡፡

**ስለ ፍቅር**

*መረቅ የፍቅር መፅሐፍ*

ፍቅር የተገለፀበት እውነት ልብ ያሳምማል፡፡ ፍፁም ነው፡፡ ልጅነት ነው. ..በንፁህ ልብ በቀላል አዕምሮ...በጉልምስና በብዙ ወጣገባ...በምስጢር በህልም... በበሰለ ህሊና በጠነከረ ሰውነት. . .በመገፋት በስቃይ በጨለማ በብቸኝነት በዝምታ....ፍቅር የመጣበት ታሪክ (story) አሳማኝ ደግሞ የሚጣፍጥ ነው፡፡ የራስ ነው፡፡ ፍቅር የሆነው መሆን ፍቅር የሚያሲዝ ነው፡፡ በፍቅር የነበሩት መልካም ጊዜያት የተገለፁባቸው ቃላት እንደ ባለክንፍ ነበሩ፡፡ በንፋስ እንደሚበሩ እንጂ በወረቀት ላይ ተጣብቀው እንደተቀመጡ አልነበሩም፡፡ ትንንሽ ልብ ያላቸው ራሳቸው በፍቅር የተያዙ. . .ፍቅር የሚያሲዙ፡፡ በፍቅር የሆኑት ስሜቶች የታዩባቸው አይኖች. . .የተነገሩባቸው አንደበቶች. . .የተመሰሉባቸው ምስሎች. . .ወደ ራስ ወደ ውስጥ ይከታል እንደማፅበል ያለ ነውጥን ይከስታል ፡፡ *ልቤን ብቻ ሆኜ ራሴን አጥቼ ብዙ ደስታ ደስ እያለኝ. . .ደግሞ እንባዬን ብቻ ሆኜ እያፈሰስኩ ስለፍቅር ህልውና እየተመሰጥኩ ብዙ ብዙ አይነት ዜማ እየሆንኩ. . . የእውነት ደስታን ተደስትኩ፡፡* መረቅ እንደ አፍቃሪዬ ነበር፡፡

**ፍቅር ስለመፍረሱ**

በብዙ ተፈጥሮአዊ እውነቶች እንዳለው ሀይል ለምሳሌ እፅዋት በአፈር መብቀላቸው ዝናብ ከሰማይ መውረዱ የማይለካ የሚመስል. . *መፈጠሩን የማይጋፋት ግድ የሆነ. .* መስተጋብሩ እንደ ባህላዊ የቡና አጠጣት ስርዓት ኪናዊ ግን ተፈጥሮአዊ የመሰለ. . . ስለፍቅር መፍረስ ያለው ሀይል ቤት እንደማፍረስ አልነበረም፡፡ *ጋራ* እንደመናድም አይደለም፡፡ አይጮህም. . .አይታይም. . .ህመም ነው፡፡

1. **ፖለቲካ**

የእውነት ግን ፖለቲካ አልነበረም. . . ሰበብ ግን ነው…ይገርማል ስለአገር የታቀደ የሚመስለው ፖለቲካ የሆነ ሰፈር ድረስ ወርዶ የሆኑ ጬጬዎችጋር ደርሶ ጎረቤታሞችን እንደ አህጉር በውቅያኖስ ከፍሎ ሲለያያቸው፡፡ *ራስ ወዳዶችን፣ ውሸታሞችን፣ ፈሪዎችን፣ አስመሳዮችን. . . ከሁሉ በላይ ግን አለመነጋገርን መደናቆርን ረገምኩ፡፡* አላዛርና ቴቢ ያላደረጉት አለመነጋገርን ነበር፡፡ የእውነት የሚደብተው የፍላጎት መለያየት ወይም አለመጣጣም ቢኖርም እንኳን መነጋገርን

ቢችሉ ሊፈርስ ያለውን መጠገን ባይችሉ እንኳን ውስጥን እንደ መጋዝ የሚገዘግዘውን ሙብሰልሰል/ሙብከንከን ይቀንሰው ወይ የለስልሰው ነበር እያልኩ እየፈረድኩ. . . *መፈቃቀርን ታዘብኩ፡፡ ነፍሴ ስለተሰበሩ ልቦች ህልሞች ጠባቃ የሆነች ያህል በሀዘን ኮሰሰች፡፡*

## 2. በሽታ

በሽታ ግን አልነበረም፡፡ በሽታ ሰበብ ነበር፡፡ የሆነው ያለፈ የመሰለ ያላለፈ ታሪክ ነው፡፡ ወሬ ነው፡፡ መገፋት ነው፡፡ ስቃይ ከተስፋ ሲበልጥ ነው እንደተራራ ከፍ ብሎ ብርሃን ሲከልል ነው፡፡ የሆነው አለመነጋገርም ነው፡፡ መምሰል ነው፡፡

እዝራም ማክዳም የሚጠሉትን የነጀሳቸውን፣ የሚሸሹትን ማህበረሰብ፣ የማህበረሰብ ወሬ ሆነዋል፡፡ ለምን አልሄደም? ለምን አልመጣችም? ለምን አልተነጋገሩም? ለምን ለራሳቸው ብቻ ያወራሉ?. . . በሁሉ የበሰለው እዝራ የማክዳ ነገር ሰለምን አልበራለትም? ብዙ ያየችው ማክዳ የወሬን ጥልፍልፎ ተምራለችና እንዴት የዋህድ ቀላል የነገር ጉንጉን አልፈታ አላት? እዝራ obsessed ያደረገው ፍቅር ሲበላሽ ከመጠገን ደግነትን ማሳየትን ለምን መረጠ?. . .ሁሉ ራስ ያዞራል. . . ሁሉ ያደክማል. . .በነሱ ቦታ አለመግባት ራስን ከቶ አለመጠየቅ ግን ያስቸግራል፡፡ በብዙ የደረጀ የህይወት ልምድ የመጣ ነበርና የእዝራና የማክዳ ፍቅር መፍረስ ከማሳዘን እኩል አናዶኛል፡፡

## ከፍቅር በኋላ

ብዙ ሀዘን ነበር ሙሾ ያልሆነ፡፡ በጥያቄ ፣ በማብራራት የተንገዋለለ፡፡ በባህሪ ለውጥ ማር ምሬት የሚልስ፡፡ በስሜት እና እውነት እና ማስረጃ እና ናፍቆት የሚተራመስ. . .በትዝታ የሚቆጣ. . .በትዝታ የሚያልቅ. . . በትዝታ የሚፈርድ የማያላዝን ትካዜ፡፡

**አጠቃሳይ ስስመፅሐፉ ይዘት**

**<u>ስልት (Technique)</u>**

መረቅ ፍፁም አዲስ አቀራረብ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ከሌሎች አላነበብኩም፡፡ በፊት በአዳም ከተፃፉት መፅሐፍትም የተለየ ነው፡፡ ከመፅሐፉ ሽፋን ስዕል ብነሳ መጀመሪያ የሆነ የአብስትራክት አይነት ነገር በውስጡ ያለ ግን ደግሞ ከመፅሐፉ ይዘት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌለው አድርጌ ወሰድኩ፡፡ አንጓ፣ መለልታና እና መረቅ የሚሉት ቃላት አይኔን ስበዋል፡፡ አንጓ አውቃለሁ መረቅ አውቃለሁ መለልታን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማሁ፡፡ ሶስቱ በቅንብር የአገዳ ገላጭ መሆናቸውንም ለመጀመሪያ አስተዋልኩ፡፡ እውቀት ነበር፡፡ ወደ ውስጥ ገብቼ የቴክኒኩ ነገር ሲገባኝ ማለት በ highlighter ያሉት ቃላት እንደመረቅ መወከላቸው ከዛም ካሉበት የገፅ ቁጥር ጋር በማስተናበር የ mathematics አይነት equation ቀምሮ በአንጓ መለልተና መረቅ ማጠቃለል የእውነት አስደነቀኝ፡፡ አንድ አጠቃላይ የስራው ሀሳብ ሁለት ክብደቱ ማለት ሀሳቡን በተግባር ለማዋል የሚጠይቀው ጊዜ፣ ትዕግስት ባጠቃላይ effort ፡፡ ስለዚህም በስያሜ መረቅ የተባለው መፅሐፍ እንደመረቅ የነጠረ ነገር ወካይ ሳይሆን ራሱ ህይወት እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ልዩ ነበር፡፡

በመረቅ በተግባር የሆነዉ በተለምዶ መጽሐፍ የመንፈስ ምግብ ነው የሚሉትን ህይወት ሰጥቶ በአፍ የሚገባ ምግብ ማድረግ ነው፡፡ ታዲያ ስገልጠው የሚመስለኝ የሽፋን ወረቀቶቹ እንደ እንጀራ፣ እኔ ያንን አመሳቅሎ የያዘዉ እጄ ወይም ያስቀመጥኩበት ጠረጴዛ እንደ ትሪ፣ ከዛ ሁሉ ቃላት እንደ ወጥ (በጣም እንደሚጣፍጠኝ አይነት ወጥ) የጠቆሩት ቃላት በእዉነትም እንደመረቅ እንጀራውን የሚያርሱ. . .ሳነብ. . .ስበላ. . . ጉርሻ ስጠቀልል. . .ሳስገባ. . . ክብደት ሆዴን ሲሰማኝ. . . ስጠግብ. . .ስጨርስ. . .ለራሴ ስተረጉም. . ለራሴ ስተነብይ… የጣት አሻራዎቼ በመረቅ ያለው የነአላዛር ልምድ ነው፡፡ የነእዝራ ትንተና ነው፡፡ የነማኪ መንገድ ነው. . . የቴቢ ህይወት ነው፡፡ ሁሉ አዲስ አይነት እውቀት ነው፡፡ ስለአገር የሆነ ስለ አገሬ ሰዎች የሆነ. ..ስለሰው ልጅ የሆነ፡፡ ስለወስጤ ስለራሴ የሆነ፡፡ በዚህም ደፍሬ እንዲህ ስሜቴን አጠቃልላለሁ፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ እንዳነበብኳቸሁ ብዙ ያልሆኑ ቁም ነገሮች እውቀትን፣ እውነትን ፣ አዲስ ነገርን እንደገለጡልኝ ከመለኮታዊ ክብደታቸው ባሻገር እንደ መረቅ ከአንድ ወይ ከሁለት ሌሎች መፅሐፍት (Khahlil Gibrans) በቀር በእውነት ፣በታሪክ (Story)፣ በስሜት ውስጤን የፈተሸ የለም፡፡ እንደ ካርታ ነበር፡፡ መንገድም ጉዞም ነው፡፡ በወጣ ገባው ደክሜአለሁ፡፡ የረጋ ነው ያልኩት ስስ እውቀቴ ተናውጧል፡፡ ማስተዋሌ እንደባለ አይን አተኩሯል፡፡

**ስለ ህጽናዊነት**

በመጀመሪያ ህጽናዊነት የሚያስደንቀኝ ነው፡፡ በሀሳብ ምጥቀቱ እንደ ዛፍ እንደ ቅጠል ተፈጥሮአዊ መሆኑ፡፡ የሰዎች ግንኙነት የሰው ልጅ ዘር ቀጣይ እንዲሆን እንደ ውሀ እንደ መሬት እንደ እሳት እንደ እህል ያለ element ነው፡፡ ሀይል ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ቀጥታ ሳይሆን መረባዊ መሆኑን ለማሳየት መሞከር ወይም በዚህ እሳቤ ነገርን መጠንሰስ ከአዋቂነት ነው፡፡ መፅሐፎችን(novels)) ሳነብ በተረት ነውና የጀመርት ታሪኩ ያጓጓኛል፡፡ ከዛ ባለፈ ግን የታሪኩ ይዘት (essence) ዋናው ጉዳዬ ይሆናል፡፡ ማግኘት የምፈልገውን ማየት ያለብኝን ፀሐፊው ሊሰጠኝ ያሰበውን በዛ አያለሁ፡፡ ታሪክ (Story) ሳይሆን ስሜት፣ ለነገር ያለን ዋጋ፣ የምናይበት አተያይ ሁሉ በይዘቱ በኩል ይመጣል፡፡ የሚለያየን የሚያመሳስለን ግራ የሚያጋባን . ..ምናምን. . . ታዲያ ታሪካችን መንገዳችን፣ ኑሮአችንን መገኛችን ይለያይ እንጂ የሰው ልጆች ሁሉ ውስጣችን ባለ ይዘት አንድ ነው፡፡ ይሄ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ አዳም እንደ explorer ይሄንን ነው explore አድርጎ ሊያሳየን የሚጥረው፡፡ ህፃናዊነት ብሎ፡፡ አዳም በአስተውሎቱ እንደ ፈጣሪ ቀማሪ ነው፡፡ ይህ ያስደንቀኛል፡፡ ሌላ ህፃናዊነት ለሁሉም ነው፡፡ የሁሉም ነው፡፡ መፅሐፍትን ከብቸኝነት ለመገለል ይጠቅማል ተብለን ብቻችንን ሆነን ጊዜን ለመግፋት በሚል እሳቤ ብዙዎችን ማንበብን ተለማምደናል፡፡ ከመፅሐፍ ጋር ለሚያየን ብቻችንን ስለምንመስል መፅሐፍት በተለይም novels የሚያነብ ብቸኛ ነው የሚል ግንዛቤ በብዙ ሰዎች እስኪፈጠር ድረስም ሆኗል፡፡ ህጽናዊነት የመፅሐፉን ግለታሪኮች በሀሳብ በቁስ በስሜት በማስተሳሰር፤ አንባቢን በይዘት (essence) ከባለታሪኮቹ ጋር በማገናኘት፤ ይልቅም መፅሐፉን እንደምግብ የሚበላ አድርጎ በማቅረብ ብቸኛ አንባቢ ሳይሆን የመፅሐፉ አካል የመፅሐፍ ባለቤት መሆናችንን ያስረዳናል፡፡ ለብቻ የሆነ ታሪክ የለም፡፡ ለብቻ የሆነ ስሜት የለም፡፡ እንደ ደሴት የሆነ ሰው የለም፡፡ ይሄ አፅናኝ ነው፡፡ ፈዋሽ ነው፡፡ መውደድ ነው፡፡ አሳቢነት ነው፡፡ ጓደኝነት ነው፡፡ ደስታ (Enjoyment) ነው፡፡ ያስደንቀኛል፡፡

በመረቅ ከሁሉ መፅሐፍት በተለየ ህጽናዊነት በብዙ መልክ ወይም መንገድ ልክ ደም ወደ ተለያየ አካላችን እንደሚያደርገው አይነት ፍሰት ሆኖ ይፈሳል፡፡ የእናኑ ጥፍር ና ቴቢ፡፡ የቴቢ አልበም እና ማከዳ፡፡ የማከዳ የህልም ጥሪ እና እዝራ፡፡ የእነ ቴቢ የ balloon ትርዒት እና የአላዛር ተመሳሳይ የመሰለ የፊኛ ምልከታ፡፡ የአላዛር የእስር ክፍል እና ፅሁፍ እና ቴቢ፡፡ የማከዳ የቤላ እና የአልማዜ የአይን ላይ ስሜት፡፡ የአላዛር እና የዘውገ እና የአንተ አለም ዝም ብሎ የመሰለ የልጅነት ጊዜ ወሬ እስከ ማከዳ ፡፡ ቴቢ በረከት ነጋሲ አላዛር፡፡ የቴብ የዶሮ ላይ አትኩሮት እና የአላዛር ዶሮታ፡፡ መዓት ነው፡፡ ህጽናዊነት ሀሳብ ቁስ፣ ስሜት ህልም እየሆነ ግለ ታሪኮችን በጥብቅ ያገናኛል፡፡ አንባቢንም ከየትኛውም መፅሐፍ በበለጠ በስሪቱ ምግብ ሆኖ ወደ ውስጡ ይገባል፡፡ የታሪኩ ተጋሪ ያደርጋል፡፡ የቴክኒኩ መገለጥ እንደተወሳሰበ መረብ ለውጭ አይን ቀላል አይሆንም፡፡ ማስተዋልንን ማገናዘብን ይጠይቃል፡፡ በዚህም ያነቃል፡፡ ደግሞም ስለግንኙነት ቀላል ያልሆነ መረባዊነት በተግባር ይመሰክራል፡፡ ይሄ ንቃት ያዝናናል፡፡ ወደፊት ወደኋላ ያንሸራሽራል፡፡ በሀሳብ ደግሞ physically የመፅሐፉን ገፆች በመገለባበጥ፡፡ ለምሳሌ አላዛር ሲጨርስ ስለፊኛዎቹ ያነሳል፡፡ ፊኛዎች አሉ፡፡ ቴቢ ስትጨርስ የመስኪ ፊኛዎች አሉ፡፡ በዚህ ተነገኝተዋል፡፡ ይሄን ግንኙነት አንባቢው ሄዶ ካልፈተሸ በማስታወስ ለመመስከር ይቸገራል፡፡ ስለህጽንነት አስቦ

አተኩሮ ለተመለከተ ፊኛዎቹን ያገኛል፡፡ ይሄ አንድ ያዝናናል፡፡ ማለት እንደ እንቆቅልሽ አይነት ጨዋታ ይሆናል፡፡ ሁለት ያመራምራል፡፡ ለራስ ጨዋታ ቦታ ይሰጣል፡፡ ስለ ባለታሪኮች ሊገለፅ ወይም ተገልፆ ያልደረሰ የሚመስል ስሜት በትክክል እንዲሰማን ያደርጋል፡፡ ለኔ የሆነው እንደዛ ነው፡፡ የሁሉ ማብቂያ እንደወና (Vacuum) የሆነ ህልውና (presence) ይይዛል፡፡ ባይሞትም እንደመሞት፡፡ ይሄ ቀላል አይደለም፡፡ እውቀት ነው፡፡ እውነት ነው፡፡ ብዙ አይነት ስሜት ነው፡፡ ጥበብ ነው፡፡

**አሳዛር ቴቢ እዝራ ማክ (TEAM መረቅ)**

**አሳዛር**

የአላዛር ተወዳጅ ሆኖ መቅረብ ያሳምናል፡፡ በጣምም ወድጄዋለሁ፡፡ ንጹህ አፍቃሪነቱ ---- ነገሮችን በዝምታ ማጤኑ .... የሚመዝንበት እይታ ..... ግልጽነቱ የታየበት ሁኔታ ለነገሮች ይባስም ለሚወደው ነገር ጥልቅ ስሜቱ እና የሚገልጽበት መንገድ... ስለአመነበት ነገር ሙጥኝ ማለቱ...ደግሞ ትንተናው... አል(Al) እንደ central protagonist ቀጥታ የታሪክ ማእከላዊነትን እንደ ጀግና (hero) ወይም ቀትተኛ ተረክ እንደሚጨበጥ (concrete) ባለ የተለመደ የአተራረክ መንገድ ሳይሆን ይልቁንም የስሜት እና የመረዳት ሞረድ ሆኖ በተፈጥሮው ሰልቶ በመንገዱ ተስሎ እይታችንን ይቀርጻል፡፡ሌሎች የመጽሀፉን ባለታሪኮች እንደ መስታዎት በእሱ ስል ነጸብራቅ (Reflection) እንድናይ ክፍት ወይም አሳላፊ (permeable) ተፈጥሮን ሆኖ ቀጥታ ሳይሆን ደግሞም ሳይዞር በአይን የተወሳሰበ የማየት ሂደት ውስጥ ሌንስ ያለውን አይነት ቦታ ሁነት እና ግዴታ ተክቶ ለእይታችን ብርሃንን ያሳልፋል፡፡ ታሪኩ ተዘግቶ የሌሎች ቢከፈትም በስሜት ጓዳችን ቀዳዳ እያበጀ ብርሃን ነው እና ይታየናል......አንዘነጋውም፡፡

**ተባረኪ**

ተባረኪ የምር በርበሬ በመጀመሪያ ያናደደችኝ፡፡ እየተረዳኋትም ያናደደችኝ ደግሞ ብዙ ውስጤን ያየሁባት፡፡ ለአላዛር ወግኜ ነፍሴ ከሱ ጋር አብራ ኮስሳ እናቴ ትደነቂያለሽ ብላ ስትጀምር ወደ እሷ አለም መግባቴን ደግሞም እንደማምናት አውቃለሁና እሷን ከማወቅ ቀድሜ በደራሲው ስራ ተባሳጭቻለሁ ማለት ሰራልኝ ምናምን እያልኩ፡፡ አላዛር ሲበዛ ወደ እሱ ወስዶኝ ነበርና ቴቢን የማንበብ ጉጉቴን በብዙ ድብርት ጀመርኩ፡፡ ህይወት እንዲህ ትሄዳለችና በሁለቱም ናትና በራሴ ሳቅኩኝ። ተባሪኪ አሳዛኝ ብዙ እውነት ያላት ምርጥ ነበረች፡፡

ስልጣኗ ለራሷ ነበር፡፡ በፍቅሯ የወሰነ ... በሰውነቷ የወሰነ፡፡ ቆራጥ የሆነ፡፡ የሀገሯ ማሳያ ናት፡፡ ቴቢ የምትጨበጥ አይነት ናት፡፡ ማለት ከብዙ አንጻር የእሷ የውስጥ ስሜት እና ሁለንተና ከሌሎቹ በተለየ በደንብ የተገለጸች ሆና አግኝቻታለሁ፡፡ አላዛር ሁሉው በጣም ብዙው በሷ እና ስለሷ ነው ከእናቱ ከጸሐይ ከአባቱ በቀር፡፡ ስለራሱ ይብሰለሰላል እንጂ የሚነግረን ብዙ እሷን ጥቂት እሱን ነው፡፡ እዝራም በብዙ ወሬዎቹ መሀል ያነሳታል እስከ ማከዳ፡፡ ራሷ ጥቂት ስለ አላዛር ብዙ ስለ እሷ ትናገራለች እኛ አላዛር እንደሆነን ሁሉ፡፡ አላዛር ስለሷ በበቂ ያላወቀውን ሁሉ እንደትውውቅ መአት ትነግረናለች፡፡ ደግሞ risk taker ናትና ከሌሎቹ በተለየ አንድ አይነት የስሜት ማጠቃለያ ሊኖራቸው ቢችል እንኳን ብዙ መንገዶቹን ታሳየናለች ከፍቅር እስከ ፓለቲካው....ከአገር አገር (አዲስ፣ ደዝ፣ አዋሳ) አዲስ ባህሪ አዲስ ህይወት ትዳር ..... ልጆች .... ተባረኪ ስለዚህ ሁሉን ናት .... ሰፊናት፡፡ አላዛር ተባረኪን ብቻ ነው፡፤ ውስን ነው ልክ በማጉያ መነጽር ውስጥ እንዳለው ውስንነት፡፡ የእይታ አድማስ መወሰን ሳይሆን ቴቢ እንደ ማያ ኮረብታው...

ቴቢን ስጨርስ ብዙ ድብርት ነው፡፡ ማለት ብዙ ስብራት ነው፡፡ መልሼ ወደቀጣይ ክፍል ለመሄድ ጌዜ ወስዶብኛል፡፡

**እዝራ የሰው ልጅ**

ተፈጥሮ ነው፡፡ ልክ እንደሰው ልጅ፡፡ በመጽሃፍ ቅዱሱ አዳም ቦታ መተካት የሚችል አይነት፡፡ እዝራ ድንግል ነው፡፡ እንደመሬት እንደ አየር እንደ ውሃ፡፡ መንፈስ ነው፡፡ ሰውነቱ (ስጋነቱ) ሳይሆን መንፈስነቱ ይጎላብኛል፡፡ ማለት ህልሙ ደግሞ የፍቅሩ ነገር፡፡ ፍቅር ከጽጌ ፍቅር ከማከዳ ፍቅር ከተፈጥሮ፡፡ የጥብሱ ተምሳሌት ... አጠቃላይ የእንጀራው ነገር ... የህልውናው በአዕምሮው መስራቱ...ከአደራ፣ ከንግርት፣ ከፍቅር፣ ከሰውነት፣ መያያዙ፡፡ ሽሮሜዳ ምድረ በዳ እንደሆነች .... እሱም ብቻውን እንደሆነ ከዛ ግን ህይወት ከሽሮ ሜዳ ወደ አለም እንደምታድግ የሰው ልጅ የኑሮ አጀማመር ምሳሌ ይሆንብኛል፡፡ ይሄም

እንደተፈጥሮ ጥልቅ ነው፡፡

ጥብስ ቀሊል የመሰለ ግን እንደጋራ የሚከብድ ነገር ውስጡ ያለ፡፡ ፈጣሪ ለምሳሌ ውሀን ምን ታይቶት ነው እንደውሃ አድርጎ የፈጠረው? ብዙ ብዙ ነገር ይኖረዋል፡፡ የአፈጣጠሩ ውስብስብነት ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ እንደተፈጥሮ ነው፡፡ ትርጉሙም እንደዛው፡፡ ትንታኔው የመሆንን ልክ ስለሚሰጠው ቀላል ይመስላል ግን ከባድ ነው፡፡ ደግሞ ምስጢሩ የማይወራ ነው፡፡ ማለት ለተናጋሪው ባያጎልም ባይከብድም መወራቱ ከአለማው ክብደት ወይም አስፈላጊነት አንፃር የሚያሳንሰው እንዲያውም የሚያቀለው ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የጥብሱን ነገር ቢያውቁ ስንቶቹ መመገብ ይችላሉ ወይም ምቾት ይሰማቸዋል በቃ እንደተፈጥሮ ነው አናውቀውም ግን እንጠይቃለን ለመመርመር እንሞክራለን፡፡

ሌላ እንደ ሜታፎር ስናየው በአገራችን ስላለው የስነፅሁፍ ነገር መንገድ አድርጎ ስለማህበረሰባችን ብዙ የሚል ይመስለኛል፡፡ ‘’ማን ይፈራል ሂስ’’ ሂስ በቀጥታ ወደ ስነፅሁፍ ይወስደናል፡፡ ግን ደግሞ ስለስነፅሁፋችን ብቻ አይደለም፡፡ ሜተፎርነቱ በብዙ ይተረጎማል፡፡ እንደማህበረሰብ ቅኝት ወይም ትችት አይነት ይዘት መልዕክት ይተዋል፡፡

በእዝራ ብዙ ቁም ነገር ተወርቷል....ተኑሯል፡፡ ልጅነቱን ፣ ምስጢሩን፣ መንገዱን፣ ጉዞውን እናውቃለንና ቁምነገሩን አንንቅም፡፡ እራስን አራቁቶ ከፊታችን የመቆም ያክል እራሱን ዉስጡን ይዘረግፋል፡፡ ስለ አባቱ....ስለ መልኩ....ስለ ቁመናው...ስለ ህልሙ....ስለ ምኞቱ፡፡ አያፍረንም፡፡ አይፈራንም፡፡ ፍቅሩን፣ መርገሙን፣ ጥላቻውን፣ ብልጠቱን.... ሁሉን ያወራናል፡፡ እንደ ማንሸሽገዉ እንደማንሸነግለው ህሊናችን የመሆንን ልክ በኑሮው ውጥንቅጥ ዉስጥ ሆኖ ተገኝቶ ያስረዳናል፡፡

እዝራ ባለ አደራ ነው፡፡ እንደ አገር ተረካቢ፣ እንደ ዘር ቀጣይ፣እንደ ባለ ሌጋሲ…አለሙ ግን ሌላ ነው፡፡ በተፈጥሮ የሚነሆልል፡፡ የተፈጥሮ ነገር/ውበት የተገለጠለት የሚያብሰለስለው፡፡ፍቅር ውትብትቡን የፈታለት ምስጢሩን የገለጠለት፡፡ ደግሞ ፍቅር ያሰረው በምኞት በህልም በፍርሀት የተበተበው፡፡

ግንድ ልጦ መቅመስ የማያሳፍረው.... ደፋር..እብድ፡፡ ደሞ ልቡ ነፍሱ የቃተተላትን እኩያ ሰው ወድሻለሁ/ወድጄሻለሁ ማለት ቀርቶ አይኗን ማየት እንኳን የሚያሳፍረው የሚያስፈራው....ምስኪን፡፡ ዲያቆን ቀዳሽ ዘማሪ..እንደ ቅዱስ ባህታዊ፡፡ ደግሞ የወደዳትን ገላ አምላኪ/ነዋሪ ...አለማዊ፡፡ ግልጽ (መልኩን ጎባጣውን ልሙን አውሪ)..... ምስጢረኛ በህልሙ ሂያጅ፡፡ ያልተማረ ባለቅኔ....ያማረ ጥብስ ፈልቴር ቀማሪ.... የአገሩን ሰው ልብ አዋቂ፡፡ የተዛነቀ የመዘነ፡፡ እዝራ የሰው ልጅ፡፡

**ማክዳ (ማክ)**

*ማኪ ውጤት ናት፡፡ የሁሉም መንገድ ማሳያ ናት፡፡ እንደ ማስረጃ ናት፡፡ የሰቃያቸው ፈርጅ ነች፡፡ ከገንዘብ ድህነት በገንዘብ ድሀ ናት አላዛር ወይ ቴቢ ወይ እዝራ ከዚህ ውጭ ናቸው፡፡ በእውቀት ያልበሰለች ናት፡፡ ቴቢ የተመሰከረላት አላዛር "ወደ ውጭ" የሄደ እዝራ በቤተክርስቲያን ትምህርት በጎበዝ አባት የታነፀ....እሷ ምስኪን ናት የሁለት ያልተማሩ ወላጆች ውጤት፡፡ ደግሞ ባልተማሩ መሀይሞች የህይወት ጥንስሷ የተጀመረ (አልማዜ)....በፍቅር የተገፋች ነች፡፡ ወሬ ከማናቸውም በላይ ያጎሳቆላት፡፡ እህት ነች፡፡ ብዙ ሴት ወካይ ነች፡፡*

*ምሬቷ የተገለፀበት ቋንቋ አልፈስፍሶኛል፡፡እንደሷ አይነት በማስረጃ ሳይሆን በወሬ የማውቃቸው ምክንያት እንደሚኖራቸው ባስብም አላከብራቸውምና ተንትኜ ወደ እኔ ማቅረብን አልደፈርኩም፡፡ማክዳ በኔ የማህረሰብ መስተጋብር ልምድ እንደ ኑዛዜ ነበረች በመፍረዴ ያሳፈረችኝ፡፡*
*የእዝራ ነገር ቢበላሽም እንኳን እንደ ኢየሱስ አዳኝ ሆኖ የመምጣትን ያክል ትርጉም ነበረው (ወዳዋለችና)፡፡ ይህም ስለፍቅር ብዙ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡ ብዙ አስደስቶኛል፡፡ ብዙም ተከዣለሁ፡፡ የአውነተኛ ፍቅር ክብደቱ ይገባኛልና እሷ ላለፈችበት መንገድ ለኖረችው ህይወት የቱን ያክል ከባድ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ የእውነት ሀዘን ነበር ደግሞ ሲበላሽ ደግሞ የአካልም የመንፈስም ህመም ባለው ምክንያት ልብ ቅስም ሁሉ ይሰብራል፡፡ በትምህርት መበርታቷ ዩኒቨርሲቲ join ማድረጓ ህይወት ብድራቷን በ ትግልና በፅናት እውነታ ስትከፍላት ነው፡፡ ተስፋ ነው፡፡ ደግሞም ውሳኔዋ የፍቅር ውጤት መሆኑ አንጀቴን ይበላዋል፡፡ ስለ እህቷ ስለ ጎህ ስታወራ ውይ ስታሳዝነኝ፡፡ ጎህ ቃሉ በእሷ አንደበት ሲጠራ ለእሷ ብቻ የተገባ ያክል ትረጉሙ ከቃሉ የተፈጥሮ ሁነት ወካይነት አልፎ ምስጢሯን እንደሚያቅ እና እንደ ሚረዳት እንደ ጓደኛዋ ነው፡፡ ቃል ስጋ ለብሶ በደም ተዛምዶ ታናሽ እህቷን ሆኖ እንደሚጣፍጥ ስም ይጠራል፡፡ ጎህ እንደ ህይወቷ ጉዞ ተምሳሌት ነው እንደ መልኳ ቀለም ነው፡፡ ይገርመኛል፡፡*

## <u>መልዕክተ አዳም (Ethics & Values)</u>

በብዙዎች እንደበት እንደሰማሁት እና እንዳነበብኩት የአዳም ፅሁፎች መልዕክት የላቸውም የተባለ ግን በመረጃ ያልተደገፈ በሰሜትም ያልዳበረ ሀሳብ ሙሉ እውነት አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም አልደግፈውም፡፡ አዳም በደንብ መልዕክቶች አሉት፡፡ መልዕክቶች ግን እንደ ስብከት አይደሉም እንደ ትምህርትም አልቀረቡም፡፡ መልዕክቶቹ በዕይታ ውስጥ ናቸው፡፡ ህጽናዊነት ያሳያል እንጂ አይሰብከም እንዲል ያሳየናል አንድናይ ይነግረናል እንድንመርጥ አይጎተጉተንም፡፡ ያየበትን መንገድ የነገሩ መነሻ እስኪረሳን እሸት (exhaust) አድርጎ ከጊዜ frame ውጪ ሆኖ ሳይደክም ያብራራል፡፡ ጆሮ ያለው ይስማ እያለ ሳያደነቁረን ጆሮአችንን ይከፍታል፡፡ የማስተዋላችንን/የጉብዝናችንን ልክ ሳይገምት/ሳይጨነቅ ሳይንቀን ሳያሞግሰን ለሚናገረው ዋጋ ሳይተመን ሳያከብር ሳያረክስ በእውነተኝነት ስሜት ሚዛን ግን ለክቶ መቀበል አለመቀበላችን ግድም ቅርም ሳይለው እንቅጩን ያወራናል፡፡ ስሜት አለው፡፡ ማስረጃ አለው፡፡ እውነት አለው፡፡ እውነቱ የታየበት መዓት መንገድ አለው ዝርዝር አለው፡፡ ትንተናው እንደ ሳይንሳዊ እውነት ጥራት አለው፡፡ ሁሉ በማየትና በማብላላት ጊዜ መውሰድ ከራስ ጋር ነውና እንደምክር አይነት እርዳታ ሆኖ አያሰለችም አይናቅም ወግ አያጠብቅም፡፡

**በመረቅ በእነዚህ ቅንብር ቅኝቶች መልእክቶች በአንባቢው የዜማ ፍሰት ልክ እንደሚቃኙ ሆነዉ በብዙ መልክ ተሰንገው ይገኛሉ። እንደ ልብ ምት ባለ ርቀት እና አቅም ተሰድረዉ ራስን በእዉቀት እንደ ተወሰነ በመጽሀፉ ርቀት ለንባብ እንደ ተቀመጠ ተማሪ ሳይሆን በእዉነትም በሁሉም ውስጥ ያለውን በስሜት ልባስ ተጠቅልሎ እንደ መሬት ረግቶ የተቀመጠውን በቂ እዉቀት እንደሚንካካ ኮትኳች ጣት፣ ጨለማውን እንደ ሚያበራ የብርሃን ውጋገን... ቅርብ አንቂና አመላካች (**inspiring) **ሆኖ አዳም በልምዱ በእውቀቱ በትዝብቱ እውቀታችንን ይነግረናል። መልዕክት ያስተላልፋል።**

**በብዙዎች የዛ ዘመን መስካሪ ጸሀፊ ነጋሪዎች ያ ዘመን ከጭፍጨፋና ከ ደም መፋሰስ ፊቅ ባላለ መንገድ በተደጋጋሚ ተነግሮናል። በመረቅ እንደ ሀበሻ ዘር መገለጫ እስኪሆን ድረስ አምነን የተቀበለነውን ደግሞም የምንኖረውን የጥርጣሬ፣ የአለመተማመን እና ድብቅነት እና ሌላ አይነት** unpredictable **ባህሪ(**Behavior/character) **አመጣጥ ስር እና ጥንስስ በምናውቀው የያዘመን መቼት በዋነኛ መልዕክትነት እንገነዘበው እና እንፈትሸው ዘንድ እንደ መላምት ባለ አተያይ የተቀመጠ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።**